**MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION**
**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት**

**8221 Georgia Avenue, Silver Spring, MD. 20910**
**Tel: (202) 230 - 9423 ▪ Fax: ▪ www.moreshwegenie.org**

ቀን: November 20, 2014 / ኅዳር ፲፩፣ ፳፻፯
ቁጥር: MW-0036-2014

**ለተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት**

**Security Council Report**
One Dag Hammarskjöld Plaza
885 Second Avenue at 48th Street, 21st Floor
New York, NY 10017
Telephone: 212-759-9429
Fax: 212-759-4038
Email: contact@securitycouncilreport.org
**ኒውዮርክ፤**

**ከሞረሽ ወገኔ ዐማራ የሲቪክ ድርጅት**
ሲልቨር ስፐሪንግ፣ ሜሪላንድ 20910
ዩ.ኤስ. አሜሪካ

**ጉዳዩ፦ በቁጥር ‘S/2014/727’፣ በ ‘October 13, 2014[1] የወጣውን ሪፖርት ይመለከታል፤**

1. ሞረሽ ወገኔ ዐማራ የሲቪክ ድርጅት (ሞወዐድ)፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩት ፹፩ (ሰማንያ አንድ) ያህል ነገዶች እና ጎሣዎች (ብሔር/ብሔረሰቦች) መካከል በቁጥሩ ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ ፴፭(ሰላሣ አምሥት) በመቶ ያህሉን ለሚይዘው እና ለሚደርስበት በደል የሚሟገትለት ቋሚ ጠበቃ ለሌለው የዐማራው ነገድ (ብሔር) ድምፅ ለመሆን የተቋቋመ የሲቪክ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ከመስከረም ወር ፳፻ህ፭ ዓም (Sep 2012) ጀምሮ በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች፣ በሜሪላንድ ግዛት ሕጋዊነት አግኝቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ይህን ደብዳቤ ለተከበረው የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ለመጻፍ ያነሣሣንም፣ ከላይ በርዕሰ-ጉዳዩ ሥር በተጠቀሰው መግለጫ በገፅ ፴፩(ሰላሣ አንድ)፣ በአንቀፅ ፸፰(ሰባ ስምንት) የተገለፁት አረፍተነገሮች ፍፁም ከተሳሳተ መረጃ የተነሱ እና መሠረት የሌላቸው በመሆናቸው፣ በዘገባው የቀረቡትን አብዛኞቹን ዝርዝር ጉዳዮች ወደተዛባ አጠቃላይ ድምዳሜ ወስዷል የሚል ዕምነት ስላለን ነው።
2. በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የትግሬ-ወያኔ (ሕወሓት) አገዛዝ የዐማራን ነገድ በአጠቃላይ በዘር ጠላትን ፈርጆ በመተዳደሪያ መርኃግብሩ ላይ ያሠፈረ ድርጅት ነው (**አባሪ ፩ን ይመልከቱ**)። ይህ ድርጅት ለ፲፯ (አሥራሰባት) ዓመታት በሽፍትነት፣ ለ፳፫(ሃያ ሦሥት) ዓመታት ደግሞ በሥልጣን ላይ በቆየባቸው ጊዜያት በዐማራው ሕዝብ ላይ ያደረሰው የዘር ማጽዳት እና የዘር ማጥፋት የወንጀል መጠን ሊስተካከለው የሚችለው በ፪ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የናዚ ጀርመኖች በአይሁዳውያን ላይ የፈፀሙት ‘Holocaust’ ብቻ ነው። የፀጥታው ምክር ቤት ዛሬ ዓለም በምትገኝበት ለሰብአዊነት ትልቅ ከበሬታ በተሰጠበት

[1] የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት፣ ጥቅምት ፳፻ህ፯ ዓም። ኤርትራ ግንቦት7ን፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባርን፣ የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄን እና የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ስለማስታጠቋና ወታደራዊ ስልጠና ስለመስጠቷ፣ የኤርትራን ጉዳይ በሚከታተለው ኮሚቴ የቀረበ ዘገባ። ቁጥር፦ S/2014/727።

ዘመን፣ የወያኔ አገዛዝ ዐማራን በደመኛ ጠላትነት ፈርጆ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ሁሉ አቀፍ የጥፋት ዘመቻ በከፈተበትና እያንዳንዱን ተቃዋሚውን «ዐማራ ነው» እያለ በሚያሳድድበት ወቅት፤ 'ግንቦት7' ተብሎ የሚጠራው ድርጅት ዋና መሪዎች የዐማራው ሊሂቃን ናቸው ተብሎ በሪፖርቱ በዋናነት መጠቀሱ ነገዱን ለማጥፋት ቆርጦ ለተነሳው አገዛዝ «ድርጊትህ ትክክል ነው፣ ቀጥል ግፋበት» የሚል እንደምታ የሚያስተላልፍ መልዕክት የያዘ ሆኖ ስላገኘነው ድርጊቱ ከማሳሰብ አልፎ አሳዝኖናል።

3. ኤርትራን የሚገዛው የሻቢያ ቡድንም ከሥረ-መሠረቱ በፀረ-ዐማራነት እና በፀረ-ኢትዮጵያዊነት ተደራጅቶ፣ የኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ የሆነውን ክፍለ ሀገር በግንቦት ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. እንድትገነጠል በማድረግ ዛሬ አገሪቱ በጎሣ ፖለቲካ ትርምስ ውስጥ እንድትገባ ያደረገ መሆኑን ዓለም ያወቀው ሃቅ ነው። እንደሚታወቀው የሻቢያ እና የሕወሓት ቡድኖች ኢትዮጵያን የመበታተን ዕቅዳቸውን በሰኔ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ባደረጉት ጉባኤ ይፋ ባደረጉበት ወቅት በግልፅ በስብሰባው ላይ ተቃውሟቸውን ያሰሙት ሟቹ የዐማራ ሕዝብ መሪ ፕሮፌሠር አሥራት ወልደዬስ ነበሩ። ስለዚህ የሻቢያ ቡድን የኢትዮጵያና የራሱ የኤርትራ ሕዝብም አውራ ጠላት መሆኑን የሚፈጽማቸው ኢሰብአዊ ድርጊቶችና በሌሎች አገሮች ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት የጸጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ይስተዋል አንልም።

4. «ግንቦት 7» የተባለው ድርጅት በዐማራ ልሂቃን የተደራጀና የሚመራ አለመሆኑን፣ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺህ፯ ዓ.ም. ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ጥበቃ ምክር ቤት በላከው ማስታዎሻ (Memorandum to the UN Security Council, dated October 28, 2014) በይፋ አሣውቋል።

5. እኛ ባለን መረጃ መሠረት «ግንቦት 7» በተባለው ድርጅት፣ በከፍተኛ የአመራር እርከኑ፣ ማለትም፡- በሥራ አስፈጻሚው እና በማዕከላዊ ኮሚቴው ውስጥ፣ አንድም የዐማራ ነገድ ተወላጅ የለም። ለምሣሌ የግንቦት 7 ሊቀመንበር፡- ዶክተር ብርሃኑ ነጋ (ጉራጌ)፣ ምክትል ሊቀመንበር፡- አበበ ቦጋለ (ኦሮሞ)፣ ፀሐፊ፡- ሙሉነህ ኢዩኤል (ከምባታ)፣ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፡- ኤፍሬም ማዴቦ (ከምባታ)፣ እንዲሁም የአይ.ቲ. ኃላፊው ዶክተር ታደሰ ብሩ (ጉራጌ) ናቸው።

6. በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ ከ፹፱(ሰማንያ ዘጠኝ) የማያንሱ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ በነገድ/ጎሣ «ነፃ አውጭ» ስም የተደራጁ የአገዛዙ ሥርዓት ደጋፊዎች ናቸው። ሁሉም «ነፃ አውጭ ነን» ባዮች በአንድ ነገር ይስማማሉ፡- «የዐማራ ሕዝብ ጠላታችን ነው» በሚለው አቋማቸው። ይህ በአገሪቱ የተንሠራፋው ነባራዊ የፖለቲካ ዕውነታ ነው። እንግዲህ እንዲህ ዓይነት ነባራዊ ሁኔታ ባለበት አገር፣ የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ከምድረ-ገፅ እንዲጠፋ ዘመቻ ለተከፈተበት የዐማራው ነገድ ድምፅ መሆን እንኳን ባይችል፣ ተበዳዩን የዐማራውን ሕዝብ ልጆች «የግንቦት 7 አመራሮች ናቸው» ብሎ ባልዋሉበት መወንጀሉ ከማሳዘን አልፎ፣ ድርጊቱ ትክክልም ተገቢም ሆኖ አላገኘነውም።

7. ማንም እንደሚያውቀው ዛሬ የትግሬ-ወያኔ (ሕወሓት) የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መሪዎች ብቻ ሳይሆን፥ ጋዜጠኞችን፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን፣ ገዥው ፓርቲ ከሚያቀነቅነው የፖለቲካ መሥመር የተለየ አቋም ያላቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች የሚወነጅለው፥ «አሸባሪ፣ ትምክህተኛ እና ነፍጠኛ ዐማራ፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማት፣ ያለፈው ሥርዓት ናፋቂ፣ ጠባብ ብሔርተኛ፣ ወዘተርፈ» እያለ ነው። ይህንን የትግሬ-ወያኔን የተለመደ የሐሰት የክስ ስንክሣር ለፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት በቀረበው በዚህ ዘገባ ግልባጩን ማዬታችን ደግሞ «ለእብድ ገላጋይ በትር ማቀበል» ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም የዚህ ደብዳቤ ዓላማ የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት የቀረበለትን ዘገባ በአግባቡ መርምሮ ተገቢ እና ፍትኃዊ ከሆነ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ለማስገንዘብ ነው።

8. የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት «የኤርትራ ጉዳይ ተከታታይ ኮሚቴ» ዐውቆም ይሁን ሳያውቅ፣ ሆን ብሎም ይሁን ከመረጃ ማጣት፣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች፣ በዐማራው ላይ ላለፉት ፳፫(ሃያ ሦሥት) ዓመታት በአገዛዙ እየተፈጸመበት ያለውን የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ዘመቻ እንደ ተገቢና ትክክለኛ ተግባር የቆጠረው ይመስላል። ለማስረጃም ያህል ባለፉት ፳፫(ሃያ ሦሥት) አመታት በወያኔ አገዛዝ ከ፭(አምሥት) ሚሊዮን በላይ ዐማሮች በግፍ ተገድለዋል። ከዚህ ውስጥ የ፪(ሁለት) ሚሊዮን ፭(አምሥት) መቶ ሺው ዐማራ ከ፲፱፻፹፱ እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ድረስ በነበሩት ፲(አሥር) ዓመታት ውስጥ ብቻ የጠፉ መሆኑን በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት በተገኘው ውጤት መሠረት መረጋገጡን የስታትስቲክስ ባለሥልጣን ኃላፊ ወይዘሮ ሣሚያ ዘካሪያ በራሱ በወያኔ ፓርላማ ቀርባ አረጋግጣለች (**ይህን ጠቋሚ ይመልከቱ፡-**

**https://www.youtube.com/watch?v=ndSzSPskwAw** )። ፓርላማውም ይህን ተከትሎ የዐማራውን ክልል ዓመታዊ በጀት ከሕዝቡ ቁጥር መቀነስ ጋር አያይዞ ቀንሷል።

9. የሰሜን ጎንደር አምስት ወረዳዎች፥ ማለትም:- ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ሡቲት፣ ታች አርማጭሆ፤ እንዲሁም የወሎን አንድ ሙሉ አውራጃ፣ ራያና ቆቦ ወደ ትግራይ በማካለል፣ ዐማራውን በመግደልና በማሰደድ፣ መሬቱን ትግሬ እንዲሰፍርበት አድርገዋል። በእነዚህ ወረዳዎች ይኖር የነበረው የዐማራው ነገድ ተገድሎና ተሰድዶ ዛሬ በየወረዳዎቹ ከሚኖረው ሕዝብ ፺፭(ዘጠና አምሥት) ከመቶው ትግሬ እንዲሆን ሆኗል። በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩት ተገድለዋል፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩት በስደት በዓለም ዙሪያ ተበትነዋል። በእጃችን ካለው መረጃ ውስጥ ከተገደሉት ዐማራዎች መካከል የተወሰኑትን ዝርዝር **በአባሪ ፪** አቅርበናል።

10. በኦሮሚያ (ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቡር፣ ባሌ እና ሸዋ)፣ በደቡብ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ይኖሩ የነበሩ ዐማሮች፣ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት ታድነው በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል።

11. ከዐማራ የጸዱ ክልሎች ለመፍጠር በተያዘው ዐማራን የማጥፋት ዘመቻ ከ፭(አምሥት) መቶ ሺ በላይ ዐማሮች ከሶማሌ፣ ከኦሮሚያ፣ ከሐረሪ፣ ከደቡብ፣ ከጋምቤላ፣ ከቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና ከአፋር ክልሎች እንዲሁም ከራሱ ከዐማራው ክልል ጭምር ለዘመናት ከኖሩበት አካባቢ ቤት ንብረታቸውን ተዘርፈው እንዲፈናቀሉ ተደርጓል።

12. በተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች በስደት ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ በቁጥር ፷(ስድሣ) ከመቶ የሚሆነው የዐማራው ነገድ ተወላጆች መሆናቸውን አቶ ካሣሁን አየለ የተባለው በዩ.ኤስ. አሜሪካ የወያኔ አምባሳደር የነበረው ኅዳር ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. በቁጥር ዋሽ/209/98 በአድራሻ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካቢኔ ጽሕፈት ቤት በጻፈው ደብዳቤ አረጋግጧል። ይህም የሚያመለክተው ዐማራው በአገሩ ሠርቶ ለመኖር የሰብዓዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶቹን የተገፈፈ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

13. በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ላይ «፵፭(አርባ አምሥት) ዓመት ዕድሜ፣ ፳(ሃያ) ዓመት አገልግሎት» የሚል ቀመር በማውጣት፣ የዐማራውን ነገድ ተወላጆች ከመንግሥት ቢሮክራሲ መንጥረው አስወጥተዋል። በአገሪቱ የጸጥታ፤ የመከላከያ፣ የዲፕሎማሲ፣ የግምሩክና የትራንስፖርት ቁልፍ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተቋሞች አንድም የዐማራ ነገድ አባል ተፈልጎ አይገኝም። አሉም ከተባሉ አማርኛ ተናጋሪ የሌሎች ነገዶች ተወላጆች እንጂ ዐማሮች አይደሉም። «ብሔረ ዐማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)» የሚባለውን የኢሕአዴግ አባል የሆነውን ድርጅት የሚመሩት:- ኤርትራዊው በረከት ስምዖን፣ ትግሬው ሕላዌ ዮሴፍ፣ ትግሬ-አገው ታደሰ ጥንቅሹ፣ ጊሚራ-ሲዳማው ተፈራ ዋልዋ፣ ትግሬ-አገው ካሣ ተክለብርሃን ናቸው። ይህም ድርጊት ሁለት ታሪካዊ ሁኔታዎችን ያስታውሰናል። የመጀመሪያው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የናዚ ጀርመኖች በወረሯቸው ግዛቶች በገዢነት ያስቀምጡ የነበሩት የጀርመን ዝርያ ያላቸውን የናዚ ፓርቲ አባሎች የፖላንድ፣ የሩሲያ፣ የኡክራይን፣ ወዘተርፈ ስም እየሰጡ ነበር። በተመሣሣይ ሁኔታ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት በስታሊን የሚመራው የሶቭየት ኅብረት መንግሥት የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችን በተፅዕኖው ሥር ሲያደርግ፣ ሩማኒያዊ ታማኝ ሰው ሲያጡ የሩማኒያኛ ቋንቋ የሚያውቅ ሩሲያዊ ሰው የአገሪቱ የመጀመሪያው መሪ እንዳደረጉት ሁሉ፣ ወያኔዎችም ያን በቀጥታ በዐማራው ላይ ፈጽመዋል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁሉም ነገዶች በልጆቻቸው ሲመሩ በቅኝ አገዛዝ ሥር የሚገኘው ዐማራው ብቻ ነው።

14. የ«ነፃ ገበያ መር ኢኮኖሚ እከተላለሁ» በሚለው የወያኔ አገዛዝ፣ የሀብት ማፍሪያ ወሣኝ ምንጭ የሆነው መሬት በአገዛዙ እጅ ነው። መሬትን በራሣቸው ቁጥጥር ሥር እንዲያዝ የፈለጉበት ዋና ምክንያት፣ «መሬት በግል ከሆነ የዐማራው ነገድ ተጠቃሚ ይሆናል» የሚል አቋም ስላላቸው መሆኑን ሟቹ የወያኔ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ከቀድሞው የአሜሪካ መንግሥት የአፍሪቃ ጉዳዮች ኃላፊ ከኸርማን ኮኸን ጋር ባደረገው ውይይት መናገሩን ኮኸን ከኢሣት ራዲዮና ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ አረጋግጠዋል (**ይህን ጠቃሚ ይመልከቱ፣** **https://www.youtube.com/watch?v=w0nnV3S0UTw** **ከ፳፱ - ፴፩ ደቂቃ ያለውን ይከታተሉ**)።

15. እንደ ሞረሽ ወገኔ ዐማራ የሲቪክ ድርጅት እምነት፣ ባለንበት የ፳፩(ሃያ አንደኛው) ክፍለ ዘመን ላይ ቆመን፣ የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ይህን የመሰለ ግፍ በአንድ ታላቅ ሕዝብ ላይ ሲፈጸም እያየና እየሰማ፣ «ጆሮ ዳባ ልበስ» ይላል ለማለት ይቸግረዋል።

ከዚህም አልፎ ዘርን መሠረት አድርጎና ዐማራውን በአውራ ጠላትነት ፈርጆ ለ፳፫(ሃያ ሦሥት) ዓመታታት ነገዱን በማጥፋት ላይ ላለው የወያኔ አገዛዝ የፀጥታ ጥበቃው ምክር ቤት ጥብቅና ይቆማል ብለን አልጠበቅንም። ምክንያቱም ወያኔ ማነኛውንም ተቃዋሚ ኃይል ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይል የሚፈርጀው «ዐማራ ነው፣ ያለፈው ሥርዓት ናፋቂ ነው፣ አሸባሪ ነው» እያለ ነው። ይህን አባባሉን የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤትን ያህል ግዙፍና ታላቅ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ሳያጣራ «ግንቦት 7 በዐማራ ምሁራን የተደራጀ አሸባሪ ድርጅት ነው» ማለቱ፣ ወያኔ በማጥፋት ላይ ያለውን ነገድ አጠናክሮ እንዲያጠፋው ይሁንታ መስጠት ሆኖ ተሰምቶናል።

16. የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ኃይለኞች ደካሞችን፣ ባለፀጎች ንብረት-አልባዎቹን እንዳያጠቋቸው የሚከላከል፣ የሚጠብቅ፣ በዓለም ሕዝቦች መካከል ሰላም፣ ነፃነት፣ መተባበር፣ መከባበር፣ እኩልነትና አንድነት እንዲሰፍን ተግቶ የሚሠራ፤ በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈፀሙት ግፎችና እልቂቶች እንዳይደገሙ፤ በሥልጣኔና በቴክኖሎጂ ላይ የተፈጸመው ጥፋት እና ውድመት ያስከተሉት ሁለንተናዊ ቀውስ እንዳይደገሙ የሚጥር፤ የዓለም የሰላምና የመረጋጋት ዋልታ እንደሆነ ይታመናል። ይህ በመሆኑ የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት አጥፊዎችን የሚያበረታታ ሳይሆን፣ አጥፊዎችን የሚመክር፣ የሚገስጥ፣ እንዲያም ሲል ተገቢና ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ የሚመለከታቸው ክፍሎችን የሚያነቃቃ እንደሆነ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ሲቪክ ድርጅት ያምናል። የጥቅምት ፪ሺህ፲ ዓም ሪፖርቱ ግን ይህን የሚወክል ሆኖ አላገኘነውም። ምክንያቱም ለአጥፊዎች «አበጃችሁ በርቱ! በሉ!» የሚል ውሣኔ የሰጠ አስመስሎታል። ተጠቂዎች ዳግም እንዲቀጡ፣ «ማጥፋት ማጥፋት ወታደር አጥፍቷል፤ መካሱን ግን ገበሬ ይካስ» ዓይነት ፍርድ ሆኖ አገኝተነዋል።

17. ስለሆነም የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት «የዐማራ ልሂቃን የግንቦት 7 መስራቾች እና መሪዎች ናቸው፤» የሚለው ተገቢ ያልሆነውን አገላለፅ በአግባቡ መርምሮ ፍትኀዊ ከሆነ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ለማሣሰብ እንወዳለን።

የፀጥታው ምክር ቤት ለጥያቄያችን ለሚሰጠን ምላሽ በዐማራ ሕዝብ ስም በቅድሚያ የአክብሮት ምሥጋናችንን እናቀርባለን።

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ተክሌ የሻው

የሞረሽ ወገኔ ዐማራ የሲቪክ ድርጅት ሊቀመንበር